# የህወሓት ቼ ጉቬራ የወያኔ አማራ

አብርሃም በየነ

በዱር በገደሉ ፋኖ ተሰማራ
እንደ ሆቺሚኒህ እንደ ቼ ጉቬራ

ፋኖ ተሰማራ ብሎ መዘመርና ፋኖ.... ፋኖ...... ብሎ ክራር መምታት ደሮ ድሮ ቀረ። በነ "ቼ" ዘመን። "ቼ" ጠበቅ ብሎ ሲነበብ የማቾነፍ መፈክር በነበረበት ወቅት። ክራሩም እንደ ዛሬው በጅብ ጅማት ሳይወጠርና ቅኝቱም እንብላው ሳይሆን እንበለው በነበረበት ወቅት "ቼ" ዝነኛ ነበር። ያኔ ቼ በለው ሲዘፈንና እንደ ሆቺሚኒህ እንደ ቼ ጉቬራ ተብሎ ሲዘመር የኢትዮጵያን ተማሪዎች ፀጉር አቁሞ አፍሮ ያስነቅስ ነበር። ወኔ ነሽጦም፦

"ገዳይ እወዳለሁ ደፋርም አልጠላ
ሲደክመኝ አርፋለሁ ከጎፈሬው ጥላ"

ያስብል ነበር። ዛሬ ዛሬ ፋኖ ብሎ እንጉርጉሮ ቼ ብሎም መዝሙር በኢትዮጵያ መሬት ነውር ሆኗል። ያኔ የቼ በለው ቅኝት ወይም የፋኖ ቁዘማ አለያም እንደ ቼ ጉቬራ....... የሚለው ወኔ ቀስቃሽ ዝማሬ በጎዳና ሲደመጥ የነበረው ትርጉም ዛሬ ላይ ነውር ሆኗል። ነውርነቱም አንገት ያስደፋል።

እዚህ ሰሜን አሜሪካና አውሮፓ ግን ትንሳኤው "ትንሳኤ ሙታን" ሆኖ ፋኖና ፋኖነት ግነት አግኝቷል። በትልልቅ ከተሞች እርድ አንቀጥቅጥ ሰልፎች ፋኖ ተሰማራ.......... እያሉ ሲተሙ ተስተውሏል። ዳሩ ይህ የወያኔን አጋሚዶ ጦር ፋታ ነስቶ የኖረው ትግል ግን ለፍትህ ጋዜጣና ለዘጋቢዋ ለአቶ ተመስገን ደሳለኝ ባገር ቤት የዜናው ስውር መሆን ገርሞኛል። አቶ ተመስገን አንድም ቀደም ሲል ይታተሙ የነበሩትን የኢትዮጵያን ሪቪውንና የኢትዮጵያን ሬጂስተር መፅሔቶች አያነቡም ነበር። አለያም ዛሬም ቢሆን የእሳት ቴሌቪዥንንና ሬዲዮ አያዳምጡም ወይም አያዩም ማለት ነው።

" ፋኖ፣ ፋኖ፣....... የሚል ዘፈንም አይዘፈንም። የቱንም ያህል መብትህ ቢገፈፍም፣ ድምፅህ ቢጭበረበርም አንተም አታንጎራጉረው። ሌላው ቀርቶ እነዚህ መብቶች ቅንጦት ናቸው ብለን ብናልፋቸው እንኳ ቢርብህና ቢጠማህም » ፋኖ ፋኖ« አረ ፋኖ .....« ብለህ አትዘፍንም።"

ሲሉን አቶ ተመስገን ከእሳት ወሬ በእጅጉ እንደራቁ ያስረዳል። እኛ ግን ቼ በለውና ፋኖ... ፋኖ .. ካልን ዘመን የለንም። እድሜ ለጀግኖቻችን!!

ፋኖነትና ፋኖ በዛሬዋ ኢትዮጵያና በዛሬው ትውልድ የሚወደዱ ኩነቶች ወይም የሚናፈቁ ትውስቶች ላይሆኑ ይችላሉ። በዚህ በሰሜን አሜሪካና አውሮፓ ግን ፋኖና ፋኖነት የቼ ጉቬራን እግር ተከትሎ የተሰደደ እስኪመስል ነው ገናናነቱ።

የወላድ ማህፀን በድባቡ ይኑርና ከደርግ ውድቀት ማግስት ጀምሮ እስከ እዚህች ቅፅበት ድረስ ፋኖዎቻችን ወያኔን እንቅልፍ ነስተውት ኖረዋል።

ቀደም ሲል በአሥራ ዘጠኝ ዘጠናዎቹ መጨረሻ ዶ/ር አክሊሉ ሃብቴና ዶ/ር አንዱ ዓለም ሙላው በሚያዚያ ወር በሲዳሞ ክ/ሀገር በክብረመንግስት ከተማ ግንባር መስርተው በዚያው ዓመት ግንቦት ወር መባቻ ላይ ከቋራ እስከ ሁመራ( ተሰነይ ድንበር ) በወረቀት ነጻ ያወጡትን ግዛትና የማረኩትንም ተሽከርካሪ እስከነ ታርጋው አስነብበውናል።

ይህ ፈጣን እንቅስቃሴያቸው ማርኮኝ እኔም፦

ሲዳሞ ገስግሶ ቿራ ገድሎ ማደር
እንዲህን ቅርብ ነው ሲዳሞ ለጎንደር?

የምትል የስንኝ ቿጠሮ አስቋጥሮኝ ነበር። ዳሩ የነዶ/ር አክሊሉ ጦር ቀለሙና ወረቀቱ አልቆበት ሁመራ ላይ ሽብረክ ብሎ ቀረ።
ያ ትግል ለምን እንዲያ ሆኖ እንደ ቀረ ዛሬ ላይ ሆኘ ሳስበው አንድም የኛው ጠማማ እድል አይለፍላችሁ ብሎን አለያም ወያኔ ለአኩሱም ጺዎን ስለት አስገብቶ ኖሮ ስለቱ ስለሰመረለት ሊሆን ይችላል።

የሆነው ሆኖ ግን ከነ ዶ/ር አክሊሉ ኋላ ጀግና ስንፈልግ ብዙም አልባጀን። የአክሊሉን መዳከም እንደሰሙ ኮሎኔል ጎሹ ታጠቅ ብለው ተነሱ። እኛም የፍጥነታቸው ቅልጥፍና አመርቅኖን፦

አይደፈሬው የጀግና መልካ
አክሊሉ ሲወድቅ ጎሹ ተተካ

ብለን ፎከርን። ከጎናቸውም ቆምን። እርሳቸውም ባካበቱት የውትድርና ሙያ ጠሩን መርተው ባጭር ጊዜ ውስጥ የደብረማርቆስን እስር ቤት ሰብረው እስረኞችን ነጻ አወጡ። ቀጥለውም የደብረ በርሃንን ከተማ ከወያኔ አረመኔ መንጋጋ የተረፈች ባቂላ አደረጓት።

ኮሎኔል ጎሹ በሚያስደንቅ ፍጥነት መሃል አዲስ አበባ ገብተው የልደታንም ወረዳ የነጻነት ሽማ እንዳጎናጸፏት ፈጥነው "የመድህንን" ታጋዮች እኛን ሆነው አመሰገኑልን። በኢትዮጰያን ሬጂስተር መጽሔት አራት ገጽ በፈጀ ፅሁፍ።

የፍትህ ጋዜጣ ዘጋቢ ተመስገን ደሳለኝ ይህን ሁሉ አያወቅ ኖሯል መሰል ዛሬ ላይ ቆሞ ፋኖ የለም ይለናል። ሌላው ቢቀር የኮሎኔል ጎሹው ቀኝ እጅ ተጋዳላይ ቾሩ ፋንታሁን አዲስ አበባ ገብቶ " ሚሊየነሩ ታጋይ" ተብሎ በጦቢያ መጽሔት ሽፋን ላይ ሲወጣ ተመስገን ደሳለኝ ማንበብ ነበረበት።

ተመስገን ግን መጻፍ እንጂ ማንበብ አይወድም። ቾሩ ፋንታውን በጦቢያ መጽሔት ስላላነበበው ይመስለኛል ዛሬ ላይ ቆሞ በትናንቱ ትውስታ "አማራው የህወሓት ቹ ጉቼራ" ሊለን የከጀለው። ተጋዳላይ ቾሩ ፋንታው የልደታውን ድርጊያ ( operation) እንደመራው አያውቅ ኖሮ ይሆናል።

ተጋዳላይ ቾሩ ባለሁለት ጃኬት ነው። የክትና የዘወትር። የዘወትሩን በተቃዋሚወች የክቱን ግን በወያኔወች ፊት ነው የሚለብሰው። ቾሩ የሞላ የተረፈው ታጁር ነው።

የጀግና አንቱታ የለውምና ቾሩን ያክል ሰው አንተ ስል አንባቢ ቅር እንደማይሰኝ እርግጠኛ ነኝ። ሚኒሊክን እምዬ፣ ቴዎድሮስን መይሳው ካሳ ማለት የተለመደ ባህል ነው ብዬ ነው ቾሩን አንተ ማለቴ።

አዲሱ ለገሰ፣ ህላዌ ዮሴፍ፣ ሀሰን ሽፋና ሌሎችም ቱባ ቱባ የወያኔ ካደሬዎች ወደ አትላንታ ጎራ ሲሉ የእራት ግብዣ ወጫቸውን ሽፍኖ መሪዎቻችንን አክብሮ ያስከበረን ተጋዳላይ ቾሩ ነበር። ይህን ፋኖ ተመስገን ደሳለኝ አወቀው አላወቀው ለኛ ጉዳያችን አይደለም። ነብይ ባገሩ ድሮስ መቼ ተክብሮ ያውቅና?

አቶ ተመስገን ደሳለኝ ታጋዳላይ ቾሩን አወቀው አላወቀው እኛ ግን፦
ቾሩ ተቀምጦ ጎሹ ለምኔ
ሁለት እጁ ቀኝ እንደ ሽማኔ

አንድም አንድነት አንድም ወያኔ። ብለን ፎክረንለታል።

የፍትህ ጋዜጣና ዘጋቢዋ ተመስገን ደሳለኝ ግን እነዚህን ወደር የማይገኝላቸውን ፋኖዎች አለማወቁ ይመስለኛል የአማራ ወያኔና የወያኔ ቹ ጉቬራ ሲናፍቅ ዓለማቀፋዊውን ፋኖ ቼ ጉቬራን ከመንደርተኛ ሽፍታና ጌታውን ተከትሎ ዱር ከወጣ አሽከር ጋር በነፅፅር ታሪኩን ሲያክቸለችለው የሞከረው።

ያም ሆነ ይህ ግን እንደ ህዝብ እኛን ካገር ውጭ ያለነውን ኢትዮጵያውያንን እንደ ተጋይ ደግሞ አቶ ቸሩ ፋንታውን ሆኖ መገኘት ይታገሉታል እንጂ አይታደሉትም።

የሚያሳዝነው ግን ኮሎኔል ጎሹና ተጋዳላይ ቸሩ ፋንታው ጠራቸውን ያሰማሩበት ጫካና ድላቸውንም ያስመዘግቡበት የነበረው ተራራ ( የኢትዮጵያን ሬጂስተር መጽሔት) ሲከስም የእነርሱም ፋኖነት አብሮ መክሰሙ ነው።

ግና ግና ጀግና ሲወድቅ አርማውን ጀግና ያነሳዋል ሆነና ታሪካችን የኮሎኔል ጉሹን ጋሻ ኢንጂነር ቅጣው አንስቶ ዘገሩን ነቀነቀው። አፈሩ ይቅለለውና እንጂነር ቅጣው እጅጉ ለእረፍት ያልታደለውን ወያኔንና ሸንተረሩን በመትረየስ ሲያርበደብድ ነበር ሞት የቀደመው።

ብዙም ሳይቆዩ አቶ መልኬና አብርሃም ያየህ ከዴንማርክ፤ ዝግጥግጥ ብሎ ደግሞ ኮሎኔል አስራት ቦጋለ ከወደ ፓሪስ ወደ ጫካ ገቡ። ሳይውል ሳያድር ላጭር ጊዜም ቢሆን ብቸኛ የነበረው በርሃ ተጨናነቀ። የኢንጅነር ቅጣው ድንገተኛ ሞት ግን እንዲህ አስቆዝሞናል።

ከደምም ደም አለው ጣፋጭና መራር?
መሬቱ እሚበላው እየለዩ ደፋር

አሰኝቶ። የሆነው ቢሆንም ጀግና ይወለዳል እንጂ አይሞትም እንዲሉ አንዳርጋቸው ጽጌና ዶ/ር ብርሃኑ ነጋ ክፍተቱን ባጭር ጊዜ ውስጥ ሞልተውታል። እኛም በደሰታ ፈንድቀን፦

ዝናር በኪሴ ካላሽን በጁ
የፔንታጎን ምርጥ ፈረንጂ ወዳጁ
የሙት ከተማን አድማ በትኖ
ባሜሪካ አገር ዋቶ አደር ፋኖ

ብለን ፎከርንላቸዋል። የእሳት ሬዲዮና ቴሌቪዥን ግን ይህን ዜና ሳይዘግበው በመቅረቱ ቅር ተሰኝቻለሁ። ዶ/ር ብርሃኑም ቅሬታ አሳድሮ “በገዛ ዳቦዬ ልብ ልቡን አጣሁት” ሳይል አልቀረም።

በእሳት ሬዲዮና ቴሌቪዥን መቋቋም ሁላችንም ደስ ብሎናል። የእንግሊዝና የአሚሪካ መንግስታት ምስጋና ይግባቸውና እሳቱን ቀንና ሌሊት ለኩሰን ሃያ አራት ሰዓት እየሞቅን ብርዳማውን ክረምት ተወጥተንበታል።

ያ የፍትህ ጋዜጣ ዘጋቢ ግን ተመስገን ደሳለኝ ባዲስ አበባ ቁር ተጨማትሮ ውሎ ሲያደር እሳቱ አገር ቤት ስለማይደርስለት እንደ እኛ ሞቆት አለማደሩ አስዝኖኛል። ለክርሞ ግን ቸር ያድርሰን እንጂ የግንቦት ሰባት ጦር ከአስመራ ተወንጭፎ የወያኔን ቤዝ ትግራይን ነጻ ካደረገልን እሳቱን መሃል አዲስ አበባ ለኩሰን አገሩን እናቀጣጥለዋለን። ባምጽ።

ፋኖ የናፈቀውን ሕዝባችንንም የግንቦት ሰባት ጀግኖቻችን ገላውን ሰድዶ ፋኖ ፋኖ….. እንዲል ነጻነቱን ያቀዳጁታል። ተመስገን ደሳለኝም “አማራው የህወሓት ቼጉቬራ” ብሎ እንዳይፅፍ እውነተኛውን ፋኖ ዶ/ር በርሃኑንና አንዳርጋቸው ፅጌን አናስተዋውቀዋለን።

በነገራችን ላይ የዚህ ፅሁፌ መነሻው የተመስገን ደሳለኝ “ አማራው የህወሓት ቼ ጉቬራ” ርዕሰ - መጣጥፍ ነበር።

ተመስገን ደሳለኝ የተባ በእር አለው። የብእሩ ትባት ግን እውነታ ይጎድለዋል። ቀድሞውን ነገር አብተው ታከለ  በአራት አያቱ አማራ አልነበረም። የአማራን የበላይነትም ከትግሬ ጫንቃ ላይ ለማንሳት ወደ ጫካ አልወጣም። አብተው የብሄር ጭቆናን ማወቅ ቀርቶ ውሾውን ሰምቶት አያውቅም።

መደብንም ከድሃ ምኝታነት ያለፈ ትርጉም አይሰጣትም። የድብ ብሀር ከተማም  አምስት ሺህ  ሕዝብ አይኖርባትም። ያኔም ዛሬም።

አይደለም አብተው አብሯቸው በርሃ የወጡት የህወሓት መስራች አባላት እንኳ የብሄርን ጭቆናና የዴሞካራሲ መብቶችን ቁስ አካላዊ ትስስር በቅጡ የሚያውቁ ታጋዮች ሆነው አልነበረም ወደ በርሃ የወጡት።

ከኢሕአፓ ጋር የተፈጠረው ልዩነትም መንሰኤው አንዱና ዋነኛው ይህ ጠባብ አመለካከታቸው ነበር። ኢሕአፓ የብሄር ጭቆና የዴሞክራሲ መብት ነው። ባገሪቱ ዴሞክራሲ ሲሰፍን የብሄሮች እኩለነት ስለሚረጋገጥ የብሄሮች ቅራኔ ይከስማል ስለሆነም ቀዳማዩ ትግላችን ለዶምክራሲ መብቶች መከበር መሆን ይገባዋል ሲል

ወያኔ ግን ቀዳማዩ ቅራኔ የብሄሮች ቅራኔ ነው። ቀድሞ መፈታት ያለበትም ይህ ቅራኔ ነው አለ። ፈርጠም ብሎም ብሄሮች ነጻነታቸውን  ካስከበሩ በኋላ ነው ከፈለጉ በመፈቃቀድ አብሮ መኖር የሚችሉት ሲል የሻቢያን ቅኝት አስተጋባ።

ወያኔወችን ለትግራይ ናፅነት እንዲነሱ የቀሰቀሳቸውና ያደራጃቸውም ሻቢያ ነበርና (ካገር በስተጀርባ የተሰኘውን መጽሓፍ ይመለከቷል) እነርሱም ሻቢያ ያስጨበጣቸውን ተልእኮ ለማስፈፀም ነበር ወደ በርሃ የወጡት። የተለእኳቸውንም ውጤት ዛሬ በአይናችን በብረቱ እያየነው ነው።

የአብተው ታከለ ቼ ጉቬራነት ግን አስገራሚም አሳዛኝም ነው። ቼ ጉቬራ ከአንድ የጌታውን እንግት ተሸክሞ  በርሃ ከወጣ ባላገር ጋር እጅግ ወደ ታች ወርዶ የሚነፃፀር ሰው አልነበረም።

ባለቤቱ ውንድሚ ገሰሰው አየለ ወደ በርሃ ሲወጣ “ጌቶች በርሃ ሲወጡ እንዴት ብቻቸውን ትሰዳቸዋለህ?” ስላለችው የባለቤቱን ቃልና የፊውዳል ባህሉን ተከትሎ ነበር አምቻውን አጅቦ አብተው በርኸኛ ለሞሆን የበቃው።

ሌላው የተመስገን ደሳለኝ ህፀፅ የወያኔን መሪዎች የያ ትውልድ አካል ማድረጉ ነው። ያ ትውልድና ወያኔ ምንጊዜም ቢሆን የማይገናኙ ሆድና ጀርባ ናቸው። በአንድ አካል ላይ የቆሙ ሁለት ሰውነቶች።

ሆድ ብዙ ይችላል። ጀርባ ግን ብዙ ቢያሸክሙት አንድም ይመለጣል። አንድም ይጎብጣል። የጎበጠን ላቅናህ ቢሉት ይሰበራል። አፈጣጠሩ ሆኖ ጀርባ አዘውትሮ የሚያየው ድሮ ጥሎት የተጓዘውን ኋላ ኋላውን ነው። ሆድ ግን ሁሌም የኋላውን እንደ ት/ቤት የተመክሮ መገብያ እንጂ የወደፊት መመሪያ አድርጎ አይጠቀምበትም። የተፈጥሮ እይታውም ዘወትር  የወደፊቱን ግስጋሴ እንጂ እንደ ጀርባ ያለፈውን እያስታወሰ ወደ ኋላ ሲያስብ አይኖርም።

ስለሆነም ያ ትውልድና ወያኔ አበቃቀላቸው ለየቅል ነው። ዱባውና ቅሉ ባንድ መሬት ላይ በቅለው ሊሆን ይችላል። ሕዝባዊ ግልጋሎታቸው ግን ባንድ መስፈርት አይመዘንም።

ዱባው የሕዝብ ቀለብ ሲሆን ፍሬውም ኮሶ ያሽራል። ቅሉ ግን ተቆራርጦ ሽክና ከመሆን ያለፈ ሕዝባዊ ግልጋሎት ስለሌለውና ፍሬውም ስለሚኮመድድ በሕዝብ ዘንድ ተፈላጊነት የለውም። ስለሆነም የሁለቱ ታሪክ የቄሳርን ለቄሳር የጴጥሮስንም ለጴጥሮስ እንዲሉ በየፈርጁ ተፈርጆ ይቀመጥ።

መጋቢት 2004

……………………………………….//…………………………………………………….